# መራሹ ? ?

## ከዓሣዬ

እንቧይ ላይሆን ሎሚ
ቅል ላይሰብር ድንጋይ
ጅረት ኣሻቅቦ ላይፈሥ ተራራ ላይ
መሆኑን ሥናውቀው የተፈጥሮ ፀባይ
የሕዝቡን ታጋሽነት እየተነኮሱ
ሃገር ሻጭ ወያኔን በሥም ሊያሞካሹ
የሹምባሽ ባንዳን ዘር
የባዕዳንን ሎሌ ኣሉ ኣሉኝ መራሹ።

ገና ከጠዋቱ እኔ እሥከማውቀው
ደመናን ገላልጠ ጎሕ ሲፈነጥቀው
የዓድዋን ኣርበኞች ዓርማውን ተረክቦ
በእኩልነቱ ላይ ቃል ኪዳን ኣንግቦ
ብሄራዊ ኢትዮጵያን በኣንድነት ኣማክሎ
ኮርቶ በዜግነት ባዕዳንን ኣግልሎ
በጋራው ሸንተረሩ በሕዝቡ ተማምኖ
ጉርንቦ ተናንቆ ሲዋደቅ ያየነው
ዓባይ ኢትዮጵያዊው መራሹን ሥናውቀው
የባዕዳኑን ቅጥረኛ
ባንዳ ወያኔን ማነው የደባለቀው ?

በምሥራቅ በምዕራብ መልዕክት ተላልኮ
በሰሜን በደቡብ ሕዝቡ ተነሣሥቶ
ኸረ እኔሥ ታየኝ የካቲት ታድሶ
ዳሩ መሃል ሲሆን መሃሉ ዳር ሁኖ
ወያኔን ሲያደባይ ዓመጽ ተቀጣጥሎ
ተነሥቷል መራሹ ዓባይ ኢትዮጵያ
ኣዋጅ ኣሥተላልፎ ሊደገም ዓድዋ

**ዘረኛው ተነቅሎ ሃገር ነፍሥ ልትዘራ !**

03/10/2014 G C.